የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

የአፋር ክልል ዲንካራ ጋዜጣ

AFAR REGION DINKARA GAZETA

OF THE AFAR NATIONAL REGIONAL STATE

11 ኛ ዓመትቁጥር 70 ሠመራ ህዳር --- ቀን 2004 ዓ.ም	በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ	11th Year No. 70 Samara ,2011

ማውጫ

በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የልማት ድርጅቶችን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ .....ገጽ 1

አዋጅ ቁጥር 70/2004

በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የልማት ድርጅቶችን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በኢኮኖሚ ዘርፍ ያለውን ሚናና ተሳትፎ በማሳደግ የክልሉ የኢኮኖሚ ልማት ማፋጠን አስፈላጊ በመሆኑ፣

የክልሉ የልማት ድርጅቶች የክልሉን ብሎም የሃገሪቱን የልማት ስትራቴጂ በማስፈፀምና ኢኮኖሚያዊ እድገት በማምጣት ረገድ ተገቢውን ሚና እንዲጫወቱ ለማድረግ የሚያስችል አመራርና ድጋፍ መስጠት በማስፈለጉ፣

የክልሉ መንግስት የልማት ድርጅቶች ተወዳዳሪና አትራፊ ሆኖ ማስቀጠል በማስፈለጉ፣

እነዚህን አላማዎች በማስፈፀም የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የልማት ድርጅቶችን ማቋቋም በማስፈለጉ፣በተሻሻለው የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ህገ-መንግስት አንቀፅ 47 ንዑስ ቁጥር 3/ሀ/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የልማት ድርጅቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 70/2004 ተብሎ ሊጠቀስ ይላል።

2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፦

1. የመንግስት ልማት ድርጅት ማለት በፌዴራል መንግስት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 አንቀጽ 2/1 የተመለከተውን ተርጓሜ የሚያሟሉ ሆነው በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ

2. በፌዴራል የመንግስት የልማት ድርጅቶችን አዋጅ ቁጥር 25/1984 እና በፌዴራል የኘይታይዜሽንና የመንግስት የልማት ድርጅቶችን ተቆጣጣሪ ባለስልጣን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 412/1996 ውስጥ የተጠቀሱት የፌዴራል መንግስት የሚያመለክቱ አገላለፆች በሙሉ የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ይመለከታል።

3. መቋቋም

1. የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የልማት ድርጅቶች በፌዴራል የመንግስት የልማት ድርጅቶች በአዋጅ ቁጥር 25/1984 የተጠቀሱትን አንቀፆች እንደአግባብነታቸው ሙሉ በሙሉና የፌዴራል የኘይታይዜሽንና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቀጣጣሪ ባለስልጣንን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 412/1996 ውስጥ ከአንቀጽ 5-12 ያሉትን ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ የህግ ሠውነት ያለው ራሱን የቻለ የክልሉ የመንግስት የልማት ድርጅት በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።

2. ይህን አዋጅ በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ይዞታ ሥር አሁን ያሉት የልማት ድርጅቶችና ለወደፊቱ በሚቋቋሙት ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል።

3. የክልሉ መንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ባለስልጣን

የክልሉ ኘሬዝዳንት የልማት ድርጅት ተቀጣጣሪ ባለስልጣንን ያቋቁማል።

4. ደንብ ማውጣት

የክልሉ መንግስት መስተዳደር ም/ቤት ወይም ካቢኔ ለዚህ አዋጅ ማስፈፀሚያ አስፈላጊ ደንቦችን ማውጣት ይችላል።

5. ስለተሻሩና ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ህጎች

1. ከዚህ በፊት በአዋጅ ቁጥር 27/1997 ዓ.ም ተቋቁሞ የነበረው የውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ኢንተርኘራይዝ በዚህ አዋጅ ተሸሯል።

2. ይህን አዋጅ የሚቃረኑ ማናቸውም ደንብና መመሪያ በዚህ አዋጅ የተደነገጉትን ጉዳዮች በተመለከተ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም።

6. አዋጅ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በክልሉ ም/ቤት ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ሠመራ ቀን **2004** ዓ.ም

እስማኤል አሊ ሴሮ

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

ርዕሰ መስተዳደር